# ሁሉን አቀፍ የአማራጭ ሃይል የሚቋቋምበትን ሂደት ለመወያየት የተዘጋጀ የምክክር ጉባኤ

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ደጋፊዎች ህብረት፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤትና፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ በጋራ በመሆን፤ በሀገራችን ኢትዮጵያ ስላለው ሁለንተናዊ ቀውስ በመወያየት ሁሉንአቀፍ የአማራጭ ሃይል የሚቋቋምበትን ሂደት ለመምከርና ለመወያየት ሁሉንም አካላት የሚያሳትፍ ከጁላይ 2-3 በዋሽንግተን ዲሲ የአገር አድን የምክክር ጉባኤ አዘጋጅተናል።

ጁላይ 2 ከሰአት በሏላ ጀምሮ ይህን ጉባኤ ያዘጋጁት ከላይ የተዘረዘሩት አራት ድርጅቶች፤ እንዲሁም ሌሎች ተጋባዥ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ያማራጭ ሃይሉን አስፈላጊነትና ወቅታዊነት በሚመለከት በተናጠል ሀሳባቸውን ካቀረቡ በኋላ፤ ታዋቂ ግለሰቦችና አክቲቪስቶች የሚሳተፉበት ምክክር ይደረጋል። በመጨረሻም ጁላይ 3 ከሰአት በኋላ የጉባኤውን ውጤት ለህዝብ ይፋ ለማድረግ የተለያዩ የሚዲያ ተቋማትና ጋዜጠኞች በተገኙበት ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣል። ይህ ጋዜጣዊ መግለጫ በአካል፣ በስልክ፣ በፓልቶክ ክፍሎችና፣ በሌሎች በርካታ መንገዶች የሚደረግና ለህዝብ በቀጥታ የሚተላለፍ ይሆናል።

በመሆኑም መላው ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ይህ በጁላይ 3 ከሰአት በኋላ የምናካሂደዉ ጋዜጣዊ መግለጫ ብሔራዊና ወቅታዊ ጉዳይ በመሆኑ፤ በአካል በመገኘት ወይም በስልክና በፓልቶክ ክፍሎች ሂደቱን በመከታተል የመሰረት ድንጋይ የመጣሉን እና ቀጣዩን ሂደት በንቃት እንድትከታተሉ አደራ እያልን፤ በአክብሮት ሃገራዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ቀን፤** አርብ ጁላይ 3፣ 2015

**ሰዓት፤** 2-4 pm በዋሽንግተን ዲሲ ሰአት አቆጣጠር

ጋዜጣዊ መግለጫውን በአካል በመገኘት የምትከታተሉበትን ቦታ፤ እንዲሁም የስልክ ቁጥር፤ የፓልቶክ ክፍሎችና ሌሎች መንገዶችን በቀጣይ ቀናቶች እናሳውቃለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ደጋፊዎች ህብረት

የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት

የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ